የሰ/መ/ቁ.254317

ቀን 28/10/2016 ዓ/ም

ዳኞች፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፍሬገነት ወርቁ ገላግሌ - ቀረበ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፍፁም ተክሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ከሳሽ  የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ከሐምሌ ወር 2010 ዓ/ም ጀምሮ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በወር ብር 3000.00 እየተከፈለኝ በሀገር ባህል ልብስና ቅርፃ ቅርጽ  እቃዎች ሻጭነት ስሰራ የነበረ ሲሆን መጋቢት 04 ቀን 2015 ዓ.ም ያለምንም ምክንያትና ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን በማቋረጥ ወደ ሥራ ቦታ እንዳልገባ በዘበኛ ያስከለከሉኝ ስለሆነ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ ካሳ ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲወሰንልኝ እና የሥራ ልምድ እንዲሰጠኝ እንዲሁም ወጪና ከሳራዬን እንዲተኩልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ያገለገሉት ከሶስት አመት አይበልጥም ፣ደሞዛቸውም ብር 3000.00 ብር ሳይሆን ብር 2700.00 ነው፡፡ አመልካች በሱቁ ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸ ምዓለ ማአ የገ ለግልም!

ያልተፈጨ ቡና ለውጪ ሀገር ዜጎች ከመሸጣቸውም በተጨማሪ ዶላር ከጥቁር ገቢያ በመግዛት መልሳ እየሸጠች በመሆኑ ከድርጊቷ እንድትታረም በተደጋጋሚ በቃል ማስጠንቀቂያ ቢሰጣትም ለመታረም ባለመቻሏ የተሰጠ ስንብት ስለሆነ ህጋዊ ነው፤ማስጠንቀቂያ በቃል ቢሆንም ተሰጥቷታል፤ ስንብቱ ህጋዊ ስለሆነ የሚከፈላት ክፍያ የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች በምትሰራበት ሱቅ ውስጥ ቡና ስለመሸጧ አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካችን ጥፋትና ከሥራ የተሰናበቱበትን ምክንያት በአግባቡ ያላስረዱ ስለሆነ ሥንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት ካሳ ክፍያ፣የሥራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በድምሩ ብር 27,000.00 እና ወጪና ኪሳራ ብር 1500 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ እና የሥራ ልምድም እንዲሰጣቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አመልካች በሥራ ቦታ ሱቅ ውስጥ ያልተቆላ ቡና መሸጥ ክልክል ቢሆንም ይሸጡ እንደነበር ጥፋታቸው በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ሥንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚፈፅሙት ክፍያ የለም፤ለአመልካች የሥራ ልምድ ይሰጣቸው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንን የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ጥቅምት 20 ቀን 2016 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ በሰበር ቅረታቸውም በሥራ ቦታ ቡና አልሸጥኩም፣ስለመሸጠም በማስረጃ አልተረጋገጠም እንጂ ሸጬ ቢሆን እንኳን በሕጉ ያለማስጠንቀቂያ ውል ሊቋረጥ ከሚችልባቸው ምክንያት ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ እና የተከለከለ ተግባር ባለመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡት መርምሮ በግራ ቀኙ ክርክር አመልካች በተጠሪ ላይ በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ፍ/ቤቱ የአመልካች የስራ ስንብት ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሻር ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የወሰነው በበቂ ምክንያት ስለመሆን ያለመሆን ተጠሪ ባሉበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች በሚሰሩበት ሱቅ ውስጥ ሊሸጥ የሚችለውና ፈቃድም ያለው የሀገር ባህል ልብስና ጌጣጌጥ ሆኖ ሳለ አመልካች በሱቁ ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደውንና ወንጀል

የሆነውን ቡና ለውጪ ሀገር ዜጎች መሸጣቸው በማስረጃ በተረጋገጠበትና ባላስተባበሉበት ሁኔታ የተከለከለ ተግባር አልፈጸምኩም በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ አግባብነት የሌለው ስለሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡አመልካች በበኩላቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከዘህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን አቤቱታና መልስ ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በተጠሪ ሱቅ ውስጥ እንዲሰሩ የተቀጠሩት የሀገር ባህል ልብሶችንና ጌጣጌጦችን እንጂ ጥሬ ቡና እንዲሸጡ አለመሆኑ ግራ ቀኙም የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች ክርክር በሥራ ቦታ ቡና ስለመሸጠ በማስረጃ አልተረጋገጠም፤ቡና መሸጠ ቢረጋገጥም እንኳን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በሕጉ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ ያልተጠቀሰ በመሆኑ ሕገ ወጥ ድርጊት አይደለም በማለት  ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው በሚሰሩበት ቦታ እንዲሸጡ ያልተፈቀደውን ጥሬ (ያልተቆላ) ቡና ለውጪ ሀገር ዜጎች በመሸጣቸው እና ይህም በመረጋገጡ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት መሆኑን ከአቤቱታቸው እና ከሥር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህን ክርክር መሠረት ያደረገ ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኝ ምስክሮችን በመስማት መርምረዉ እና መዝነዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት የደረሰ ሲሆን፣ ጉዳዩን በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን በመመርመር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ የፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህም አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የሥራ ስንብት ጥፋት አልፈጸምኩም ስንብቱ ሕገ ወጥነው በማለት ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም በክርክራቸዉ መሠረት ያላስረዱ መሆኑን ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማጣራት ስልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት አረጋግጦ ዉሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡

_ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረም ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና የአዋጁ አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2 (4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል የሰበር አቤቱ የቀረበበት የመጨረሻ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ከሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የሕገ መንግሥቱን ዴንጋጌዎች የሚቃረን፤ ሕግን አለግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት ያልሆውን ሕግ የሚጠቅስ፤ ለክርክሩ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዲይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፤ በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፤ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ፤ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዲጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ፡ ሲሆን ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2 (4) እና 10 (ሀ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

አሁን እያከራከረ ባለው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ሱቅ ውስጥ እንዲሰሩ የተቀጠሩት የሀገር ባህል ልብሶችንና ጌጣጌጦችን እንጂ ጥሬ ቡና እንዲሸጡ አለመሆኑን ግራ ቀኙም የተማመኑበት እና በሥር ፍርድ ቤቶችም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ጥሬ ቡና በሱቁ መሸጥ ህጋዊ ድርጊት መሆኑን አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ የለም፡፡

ስለሆነም ማስረጃን ለመመርመር እና ለመመዘን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ቤት አመልካች በሥራ ቦታቸው እንዲሸጡ ያልተፈቀደ ቡና ሲሸጡ የነበረ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ አመልካች የተከለከለ ተግባር በመፈፀማቸው ስንብቱ በጥፋታቸው ስለሆነ ህጋዊ ነው፤ክፍያም አይገባቸውም ሲል ከድምዳሜ የደረሰበት ጉዳይ ሲሆን ይህ ችሎት ደግሞ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕግ አልተሰጠውም፡፡

በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ሊነቀፍ የሚችል እና በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1.የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.306769 ጥቅምት 02 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2.ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየግላቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1.መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ለግራ ቀኙ ይሰጥ፡፡

2.መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርዮአፈጸጸምዓለማአ የገለግልም!